የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

# ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጎጂ የሆኑ ወይም የመውለድን ሁኔታ የሚያውኩ ስራዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 42/2013

# ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጐጂ የሆኑ ወይም የመውለድን ሁኔታ የሚያውኩ ስራዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 42/2013

ሴት ሠራተኞች በኢትዮጵያ የተፋጠነ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸውን የተጠናከረ ተሳትፎ ከግንዛቤ በማስገባት በተለይም፤

- በሥራ ላ□ ሲሰማሩ ከተለያዩ አደጋዎችና በሥራ ምክንያት ከሚከሰቱ በሽታዎች እንዲጠበቁ ማድረግ፣
- ከባድ ከሆኑ፣ ከፍተኛ ቶልበት ከሚጠይቁና አካላዊ ጉዳት ሊያስከትሉ ከሚችሉ የሥራ ሁኔታዎች መገደብ፣ እና
- ሴቶች እናት በመሆናቸው ፣ በተለይም ነፍሰ ጡር የሆኑና የሚያጠቡ ሴት ሠራተኞችን የሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር ከሚያስከትሉና የፅንስን ተፈጥሮአዊ ዕድገት ከሚያዛቡ የሙያ ጠንቆች መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢፌዲሪን ህገመንግስት መሠረት በማድረግ ሀገሪቱ ከምትመራበት የኢኮኖሚና የማህበራዊ □ሊሲዎች □ር በማጣጣም፣ ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች □ር በማገናዘብ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አፈፃፀምን ለማጐልበት ይቻል ዘንድ አግባብነት ካላቸው የመንግስት አስፈጻሚ አካላት፣ የአሠሪዎችና የሠራተኛ ወኪሎች □ር ም□□ር በማድረግ ይህ መመሪ□ ወጥቷል፡፡

## 1. አውጭው ባለስልጣን

የሠራተኛና ማህበራዊ ቶቴይ ሚኒስቴር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377 /1996 አንቀጽ 170/1/መ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

□ህ መመሪ□ "ሰራተኛና ማህበራዊ ሚ.ር ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጐጂ የሆኑ ወይም የመውለድን ሁኔታ የሚያውኩ ስራዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 42/ 2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

## 3. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፣

1. **"አሠሪ"** ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ.377/1996 አንቀጽ 2(1) የተሰጠ ትርጉም ነው፡፡
2. **"ሠራተኛ"** ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 2(3) መሠረት ከአሠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው፡፡
3. **"ሚኒስቴር"** ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 2(4) የተሰጠ ትርጉም ነው፡፡
4. **"ከባድ ሥራ"** ማለት በደቂቃ ከ7.0 ኪሎ ካሎሪ በላይ የሆነ ሜታቦሊክ ኢነርጂ ወይም ጉልበት የሚጠይቅ የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡
5. **"ተከታይነት ያለው ሥራ"** ማለት የሥራው እንቅስቃሴ የመቋረጥ ባሕሪይ የሌለበት እና የድግግሞሽ ሂደት የሚታይበት ሆኖ አካላዊ ጫና የሚያስከትል ወጥነት ያለው የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡
6. **"ከመሬት በታች የሚካሄድ የቁፋሮ ሥራ"** ማለት ከመሬት በታች በመሳሪያና በእጅ ከሚደረግ የማዕድን ቁፋሮ እና ፍለጋ ጋር የተያያዙ ሥራዎች ማለት ነው፡፡
7. **"ነፍሰ ጡር ሴት"** ማለት መጸነሷ በህክምና የተረጋገጠ ሴት ናት፡፡
8. **"ሬ ረራ"** ማለት ማንኛውም የውስጥ አካልና ህዋስን ሰንጥቆ የማለፍ ሃይል ያለው የኤሌክትሮ ማግኔትክ ሞገድ ነው፡፡
9. **"ለጤና ጉጂ የሆኑ ሥራዎች"** ማለት ከሥራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ወይም ከሥራ ሂደት የሚመነጩና በሴት ሠራተኞች ላይ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳት የማስከተል ውጤት ያላቸው ፊዚካል፣ ኬሚካል፣ ባዮሎጂካል /ስነ ሕ□□ታዊ/፣ ኢርጉኖሚካልና ሳይኮሶሻል ጠንቆች ያሉባቸው ሥራዎች ወይም □ሥራ እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡
10. **"ካርሲኖጂኒክ ንጥረ ነገሮች"** ማለት በሰውነት ኀዋሶች ወይም ሌሎች ላይ መደበኛ ከሆነው ተፈጥሮአዊ የመባዛት ባህርይ ውጭ በከፍተኛ ደረጃ ያልተፈለገ የኀዋስ ክፍፍልና የብዜት ዕድገት በማምጣት የጤና መታወክ የሚያስከትሉ ንጥረ ነገሮች ናቸው፡፡



አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

11. **“ሙታጂኒክ ንጥረ ነገሮች”** ማለት በሰውነት ኅዋሶች ላይ ያልተፈለገ የክፍፍልና መራባት ዝግመታዊ ባህርይ በማሳየት በዘርግንድ ተሸካሚ ረቂቅ ኅዋስ ወይም ክሮሞሶም ላይ የተዛባ ተጽዕኖ በማሳደር በጽንስ ላይ አካላዊና አእምሮአዊ ቀውስ የሚያስከትሉ ንጥረ ነገሮች ናቸው፡፡

12. **“ቴራቶጂኒክ ንጥረ ነገሮች”** ማለት በሰውነት የተለያዩ የኅዋስ አደረጃጀቶች ላይ የመዛባት ባህርይ በማድረስ በዘር ትልልፍ ሂደት መደበኛ የሆነ ተፈጥሮአዊ ቅንብርን በማጨናገፍ በትውልድ የሚታይ አዕምሮአዊና አካላዊ ስንኩልነትን ያስከትላሉ ተብለው የሚገመቱ ንጥር ነገሮች ናቸው፡፡

13. **“የመውለድ ሁኔታን የሚያውኩ ሥራዎች”** ማለት የሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር የሚያስከትሉ እና የፅንስ ተፈጥሮአዊ ዕድገትን የሚያዛቡ ስለመሆናቸው በሳይንሳዊ ምርምር የተረጋገጠላቸው ካርሲኖጂኒክ ሙታጂኒክና ቴራቶጂኒክ ንጥረ ነገሮች ወይም የንጥረ ነገር ውሁዶች አገልግሎት ላይ የሚውሉበት የሥራ ዘርፍ ነው፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/1996 በሚሸፍናቸው አሠሪዎችና ሴት ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 5. ሴት ሠራተኞች እንዳይሰማሩባቸው የተከለከሉ ሥራዎች

ማንኛውም አሠሪ ሴት ሠራተኛን

ሀ. በማዕድን ቁፋሮና ከመሬት በታች በሚካሄዱ ማናቸውም የጉድጓድ ወይም የዋሻ ቁፋሮ ሥራዎች፣

ለ. ፀረ ተባይና ፀረ አረም ውሁዶችን በመቀመም በመበጥበጥ፣ በመሙላትና በማሸግ ሥራዎች፣

ሐ. አስቤስቶስና የአስቤሰቶስ ውሁድ ንጥረ ነገሮችን በመፍጨትና በመሞረት ሥራዎች እና

መ. በእርሻ ማሳዎች ውስጥ ፀረ ተባይና ፀረ አረም ኬሚካሎችን በመርጨት ሥራ ማሰማራት የተከለከለ ነው፡፡

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

## 6. ልዩ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ሥራዎች

1. በብረታታ ብረት ማቅለጫ፣ በኤሌክትሮ ፕሌቲንግና ሚካኒካል ሥራዎች፣ በባትሪ ፋብሪካዎች፣ ጨረር አመንጪ መሣሪያዎችን በሚጠቀሙ ድርጅቶች □ተሰማሩ ሴት ሠራተኞች በሥራ ሂደት ለሚፈጠሩ አየር ወለድ ንጥረ ነገሮች እና የጨረር ሞገዶች የመጋለጥ ሁኔታ ከዚህ በታች በአባሪ አንድ ከተዘረዘሩ የመጋለጫ ጣሪያ ደረጃዎች (Maximum Exposure Limits) መብለጥ የለበትም::

2. አሠሪዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩ የሥራ ዘርፎችና □እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለተሰማሩ ሴት ሠራተኞች ዓመታዊ የጤና ምርመራ ያደርጋሉ::

   ሀ. ተስማሚ መቀመጫ በሌለበት ሁኔታ ለረዴም ሰ□ት በመቆም የሚሰሩ ሥራዎች፣

   ለ. በጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ውስጥ ከደምና ከሰውነት የውስጥ ፈሳሽ □ር ቀዓተኛ ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች፣

   ሐ. የድንጋይ ወፍጮ / ካባ/ እና የድንጋይ ጠረባ ሥራዎች፣

   መ. በመንገዶች ሥራ ውስጥ አስፋልት / ሬንጅ የማፍላትና የመርጨት ሥራ፣

   ሠ. □መፀዳጃ ጉድጓዶችና የቆሻሻ ማስተላለፊያ ቱቦዎች የማፅዳት ሥራ፣

   ረ. በሥራ ባህርያቸው ከፍተኛ ቅ□ቃ□ /cold / እና ከፍተኛ ሙቀት /Hot / ባላቸው የሥራ ዘርፎች፣

   ሰ. የንዝረትና ሰውነትን የማንዘፍዘፍ (vibration) ባህርይ ያላቸው ሥራዎች፣

## 7. ለነፍሰ ጡርና ለሚያጠቡ ሴት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 6 ከተጠቀሱ ሥራዎች በተጨማሪ በአባሪ ሁለት የተ□ረ□ሩ ለሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር መንስኤ ለሆኑ ንጥረ ነገሮችና የንጥረ ነገር ውህዶች በቀዓታ የሚያጋልጡ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴዎች ለነፍሰጡር ሠራተኞችና ከወሊድ በኋላ እስከ 6 ወራት ድረስ ለሚያጠቡ ሠራተኞች የተከለከሉ ናቸው::

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

## 8. ለሴት ሠራተኞች የተወሰነ የክብደት  መጠን

1. የሴት ሠራተኞችን ጉልበት በመጠቀም የሚካሄድ ማናቸውም ክብደትን ከቦታ ቦታ የማንቀሳቀስ፣ የመሸክም፣ የሚጓጓዝ፣ የማንሳት፣ የማዉረድ፣ የማውጣት፣ የመጎተት፣ የመሳብና የመሳሰሉት ሥራዎች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን የክብደት መጠን ጣሪያ ሳያልፉ ይከናውናሉ፡፡

ሀ. እንቅስቃሴው ሙሉ በሙሉ በእጅ ሆኖ፤

1. ተከታታይነ ሳለ ሥራ እስከ 15 ኪ.ግ
2. ተከታታይነት የሌለው ሥራ እስከ 25 ኪ.ግ

ለ. እንቅስቃሴው ሙሉ በሙሉ በእጅ ሆኖ ዳገት የመውጣትና ቁልቁለት የመውረድ ሁኔታታ ባለበት፣

1. ሥራው ተከታታይነት ካለው የዕቃው ክብደት እስከ 10 ኪ.ግ
2. ሥራ ተከታታይነት ከሌለው የዕቃው ክብደት እስከ 15 ኪ.ግ

ሐ. እንቅስቃሴው ባለ አንድ እግር ጋሪ በመጠቀም ከሆነ የዕቃው ክብደት እስከ 50 ኪ.ግ

## 9. ስለ ኃላፊነት

ማንኛውም አሠሪ፣

1. ሴት ሠራተኞች ወይም ነፍሰ ጡር ሠራተኞች ወይም የሚያጠቡ ሠራተኞች ሚሰሩት ሥራ ክልከላ የተደረገበት ሆኖ ከተገኘ የሥራ ደረጃቸውንና ደመወዛቸውን ሳይቀንስ ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ የማሰራትና በጠንቆቹ ምክንያት የጤና ጉዳት ያለመከሰቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. በዚህ መመሪያ የተጠቀሱና ክልከላ የተደረገባቸውን ወይም ልዩ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን ሥራ እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ ሴት ሠራተኞች ሊያደርጉት ስለሚገባ ጥንቃቄ መረጃና ትምህርት ይሰጣል፡፡
3. የመመሪያውን አተገባበር በተመለከተ በሚኒስቴሩ የሚሰጡ ትዕዛዞችን ተፈፃሚ ርል፡፡
4. ለሚኒስቴሩ በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ የአፈጻጸም ሪፖርት ቀርባል፡፡



አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

## 10. □መተባበር ፅ□□

ማንኛውም የሚመለከተው አካል □□ም ፅለሰብ □ህ መመሪ□ ተፅባራዊ እንዲሆን □መተባበር ፅ□ታታ አለበት፡፡

## 11. ቅጣት

ይህ መመሪያ የሚመለከተው ማንኛውም አሠሪ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ ድንጋጌዎችን ቢጥስ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ስለ ቅጣት የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናኑበታል፡፡

## 12. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስትሩ የዚህን መመሪያ አፈፃፀም በየወቅቱ እየገመገመ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 13. የተሻረ መመሪያ

ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጉጂ የሆኑ ሥራዎችን ለመወሰን ነሐሴ 11 ቀን 1989 ዓ.ም. የወጣው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 14. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ 25 ሚያዝያ 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር

## አባሪ 1፡ ልዩ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ኬሚካሎች

| | |
|---|---|
| ሀ. ሜሪኩሪ | 0.05 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| ለ. ዚንክ | 1.0 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| ሐ. ማንጋኒዝ | 5.0 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| መ. ካትሚ□ም | 0.1 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| ሰ. ሊት / □ርሳስ/ | 0.15 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| ረ. አርሳይን | 0.20 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| ሠ. ካርቦን ብላክ | 3.5 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| ቀ. የብረት ኦ□ሣ□ት □□ም | 10.0 ሚ/ፅ በሜትር ኪዩብ አየር |
| በ. ኮፐር/ መቴበ/ □□ም | 0.1 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| ተ. ፎስፋይን | 0.4 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| ቸ. ናይትሪክ ኦክሳይድ | 30 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር |
| ኘ. የጨረር ሞገድ / አዮናይዚንግ/ | 3 - 5 ዶዝ ኮንሰንትሬት |

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

## አባሪ 2፡ <u>ለነፍሰ ጡር እና ለሚያጠቡ ሴት ሠራተኞች የተከለከሉና ለሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር መንስኤ የሆኑ ንጥረ ነገሮችና የንጥረ ነገር ውህዶች</u>

- **አስቤስቶስ /Asbestos/**
- **አክሪሎናይትራይል /Acrylonitrile /**
- **አንቲሞኒ / Antimony /**
- **አዮናይዚንግ ሪዲዬሽን / Ionizing radiation /**
- **አርሴኒክ / Arsenic /**
- **ቦሪክ አሲድ / Boric Acid /**
- **ቤንዚን / Benzene /**
- **በሪሊ□ም / Berylium /**
- **ካትሚ□ም / Cadmium /**
- **ካርቦን ሞኖክሳይድ / Carbon monoxide /**
- **ካርቦን ዳይሰልፋ□ት / Carbon disulfide /**
- **ካርቦን ቴትራክሎራይድ / Carbon tetra chloride /**
- **ክሎሪኒትድ ሃይድሮካርቦንስ / Chlorinated Hydrocarbons /**
- **ክሎሮቤንዚን / Chlorobenzene /**
- **ኮባልት /Cobalt/**
- **□ሎሮ□ርም/Chloroform/**
- **□ሮሚ□ም እና የክሮሚየም ውሁዶች /Chromium & Chromium Compounds/**
- **ቴ□ሜታይል □ርምአልዲሃይድ /Dimethyl Formaldehyde/**
- **ኢፒክለሮ ሃይድሪን /Epichlorohydrin/**
- **ኢታይሊን ዳይአሚን ቴትራአሲቲክ አሲድ/Ethylene diaminetetraacetic/**
- **ኢታይሊን ዳይብሮማይድ /ቴ□□ለራ□ት/Ethylene dibromidedichloride /**
- **ኢታይሊን አክሳይድ /Ethylene Oxide/**
- **ክሎሮፍሎሮሜቴን /ፍሪዮን/ /Chlorofloromethane/**
- **ሊት እና ሊድ አክሳይድ Lead & Lead Oxide**
- **ኒኬል / Nickel/**

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

- **ናይትረስ ኦክሳይድ / Nitrous Oxide /**
- **ማንጋኒዝ / Manganese /**
- **ሊቲ□ም / Lithium/**
- **ሜርኩሪ /Mercury /**
- **ሜታይል ኢታይል ኪቶን /Methyl ethy ketone/**
- **ሞሊቢቴነም ትራይኦ□ሳ□ት /Molybdenum trioxide/**
- **ናይትሪክ ኦክሳይድ / Nitric Oxide/**
- **ፐርክሎሮኢታይሊን /Perchloro ethylene/**
- **ፊኖል /Phenol/**
- **□ስ□ረስ / Phosphorus /**
- **ፓሊክሎሪኔትድ ባይፔኒልስ /Polychlorinated biphenyls/**
- **ቶሉን /Tolune/**
- **ትራይክሎሮኢታይሊን /Trichloro ethylene/**
- **ቲታንየም ዳይኦክሳይድ /Titanium dioxide /**
- **ቪኒል ክሎራይድ /Vinyl chloride/**
- **ዛይሊን /Xylene/**
- **ዚንክ ክሎራይድ /Zinc chloride /**

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር